# ጠብቁ!

የግራዚያኒው ቡችላ- አንት ውሻ ጥርሳም፤

አፍ ሙሉ መርዝ ልጋጋም፤

አንት ሾተላይ ነብሰ-ጡር ገዳይ፣

ትውልድ ገለህ የሞትህ፣

ደም ጠጠህ ደም የተፋህ፣

በራስህ በደል ተበደልህ

የታሪክ ትቢያ የሆንህ፣

ሙተህ የሞትህ

በታሪክህ የከሰርህ፣

ላትድን የምትንቀሳቀስ ተውሳክ፣

ዕቃ ብናጣ አብረህ ቀረብህ፡

የምንጠላውን ጠላሁ ብለህ

የምንወደውን መስለህ።

እንዴት ይካድ ያ ትውልድ

በታሪኩ ላይ ታሪክ ይጻፍ?!

እንዴት ያንባ የገዳይ ብእር

የሃኬት ታሪክ ሊጽፍ?!

እንዴትስ ይድፈር ፋሽስት …

ቀና ሊል ከመቃብር፣

መርገሙን ሊገለብጥ፣

በአደባባይ ሊቆም

ምለን የቀበርነው ሰማእት ነኝ ሊለን?!

የጊዜ ጉዳይ ሆነና - ነግቶ እየመሸ፣

የቀረበው እየራቀ - ያልታሰበው እየሆነ፣

ተበዳይ አርምሞ - በዳይ አፍ አውጥቶ፣

ክሃዲ ለገዳይ ለመመስከር ቆሞ፣

ገዳይ ለክሃዲ የገቢ ምንጭ ሆኖ፣

ብር ቦታ ይዞ ታትሞ ታጭቆ፣

እውነት ቦታ አጥታ አየናት እነሆ!

ግን እኮ…

የተፈጥሮ ጉዳይ ነውና

መሽቶ አይቀርም ይነጋል፣

ጨለማውን ስናልፍ ጎሕ ይቀዳል፣

የአራዊቱ ጫጫታ ጸጥ ይላል፣

ጠብቁ…!

የውሸት ጊዜ አልፎ

የእውነት ጊዜ ነገ ይመጣል፣

ሕዝባችንም ፍርድ ያገኛል - ኢትዮጵያን ደስ ይላታል፣

ለዚያ ጊዜ ያብቃን!!

////////

ደርቤ ሞገስ (ከምድረ አውሮጳ)